# አለቃ ምላት ሀብቴ፤ ሕይወታቸው፣ ታሪካቸውና አበርክቶአቸው

አሻግሬ አምጤ (ዲ/ን)

**Abstract**

The object of the study is to give readers a glims of Alka Milat Habtie, one of the EOTC well-known scholars. The live of Aleka Milat simply shows how the Church has been consistently producing influencial scholars who have brought innovative ideas to the institution and the country as well. His bibliogaphy was written in a fragmented form by few scholars such as Tsehafie Tiezaz Gebre Sellase Wolde Argay, Hiruy Wolde Sellase, Lema Hailu, Admasu Jembre, Krapf, Sirgew Hable sillase and others. Aleka Milat started his religious education in his native place and expanded it to different places Aleqa Lema Hailu says that even though Aleqa Milat learned Zema, qine and the four interpretation books, he had a special love for qine. That was why I was motivated to study about him. Because, I believe, studying educated and influencial scholars like him may benefit new and young Christian scholars, both interms of their religious career and personal humble life. The source of the study is mainly secondary. Data have been collected from chronicles, travelles of European explorers and other sources. There are two reasons why my sources of information are only archives. The first reason is that I was unable to find informants and respondents who knew the scholar. The second reason is that even though I knew the availability of considerable information at Ankober Michael Church, where he taught for many years. Yet I could not rich the place because of security reasons. The findings show how influencial he was and how big his contribution to the Church was in terms of his teachings and personal life.

**Key words** – biography, scholar, Ankober, EOTC, contribution.

## ፩. መግቢያ

የአለቃ ምላት ሀብቴን የግል ሕይወት መሠረት አድርጎ የተደረገው ይህ ጥናት፣ ክፍሉ ወይም መደቡ ከግል የሕይወት ታሪክ ጥናት (biography) ጋር የሚገባ ነው:: ነገር ግን እንዲህ ያለው ጽሑፍ ሙሉ ለሙሉ የሕይወት ታሪክ ብቻ እንዳይባል መንፈሳዊ ጉዳይ ስለአለው በተወሰነ መልኩ ከሥነ ገድል ጥናትም (hagiography) ጋር የሚመሳሰልበት ሁኔታ አለ። የሕይወት ታሪክ, አንድ ሰው/ጀብደኛ/ቅዱስ ከልደት እስከ ሞት ድረስ ያሳለፈውን ፈተና፣ የወጣ የወረደበትን ጉርብጥብጥ ጉዞ፣ የደረሰለትንና የደረሰበትን፣ ያደረገውንና የተደረገበትን፣ በጥቅሉ ዋና ዋና የሕይወቱን ክፍል በጊዜ ቅደም ተከተል የሚተርክ ጽሑፍ ነው (በአማን፣ ፳፻፲፪፣ ገጽ ፲፭)።

የአለቃ ምላት ታሪክ፣ ከዚህ በተቃረነ መልኩ፣ በበቂ ሁኔታ ተጽፎ ለትውልድ ተላልፏል ለማለት አያስደፍርም። እስከ አሁን በጽሑፍ የሚገኘውም ቢሆን በልዩ ልዩ ጸሐፍያን በእግረ መንገድ ተሞነጫጭሮ የሚገኝ እንጂ ሥርዓት ባለው መንገድ ባንድ ተሰንዶ የሚገኝ አይደለም። አለቃ ምላት ሀብቴ የሃይማኖት መምህር ብቻ አለመሆናቸውን የምንረዳው ታሪካቸውን ስናነብ ነው። የተወለዱት ሞረት አቡነ ዜና ማርቆስ አካባቢ ይኖሩ ከነበሩ የሞላለት ቤተሰብ ቢሆንም ሥጋዊ ድሎት ያላሸነፋቸው ሊቅ ነበሩ። ሊቁ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ ብለው ያምኑ ስለነበር ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ ብለው በሚያምኑ መምህራን ጫና ለስደት ይዳረጉ ነበር። ቢሆንም ብዙውን ዘመናቸውን ያሳለፉት ታፍረውና ተከብረው ነው። በአማን ነጸረ (በአማን፣፳፻፲፪፣ ገጽ ፻፹፬) የሚከተለውን ይላል፤

> *ሃይማኖታቸው ምክንያት ከአንኮበር ተሳደው ሞረት ዜና ማርቆስ ተቀምጠዋል። ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የፈጸሙት ተገቢ ያልሆነ ተግባር ጸጽቷቸው ወደ መምህርነት መልሰዋቸዋል። ዐፄ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት በነበሩበት ዘመን ምላት ሀብቴን ጳጳሱ አቡነ ሰላማ እልቅና ቢሾሟቸውም በሸዋ ገንነው በነበሩ ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ ባይ ወገኖች ይሳደዱ የነበሩ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ የሚሉ ሊቅ ነበሩ። በጸጎች ቢገፉም በዘመኑ ሸዋ ወደ ነበሩት ወደእነ ክራፕፍ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ሳይሳቡ ጸንተው ኖረዋል።*

በሃይማኖታቸው ምክንያት“ የተባለው “በተዋሕዶ ከበረ” ብለው ያምኑ ስለነበር በዘመኑ በሸዋ ገንነው በነበሩ የጸጋ ልጅ ባይ መምህራን መሰደዳቸውን ለማመልከት ነው። ዐፄ ዮሐንስ ከአስመጧቸው አራት ጳጳሳት መካከል ለሸዋ የተሰጡት አቡነ ማቴዎስ፣ ከእርሳቸው ቤት እንዲያርፉ የተደረገው ንጽሕና የሚወዱ ሊቅ ስለነበሩ ነው። ንጉሠ ነገሥቱንና የሸዋውን ንጉሥ በማስታረቅ የክርስቲያኖች ደም በከንቱ

እንዳይፈስ ሃይማኖታዊና ምሁራዊ ሚና ተጫውተዋል። —ክፉ ቀን“ እስከ ተባለው ዘመን ድረስ በሕይወት መኖራቸውን የሚጠቁም መረጃ ቢኖርም ከዚህ ዓለም መቼ እንደተለዩ የሚያሳይ ትክክለኛ መረጃ አላገኘሁም። አለቃ ምላት ዕድሜ ዘመናቸውን ሲያስተምሩ፣ ለተጨነቀ መፍትሔ ሲሰጡ፣ የተጣላ ሲያስታርቁ በመኖራቸው ሕይወታቸው ለነገረ ሃይማኖት ለታሪክ፣ ለሥነ ጽሑፍ፣ ለሕግ፣ ለማኅበረሰብ፣ ለባህል ጥናት መነሻ ይሆናል። ይህን ጥናት ያደረግሁበት ምክንያት የአለቃ ምላት ሀብቴን አስተዋጽኦ ትውልዱ አንብቦ እንዲረዳው ነው። ጥናቱ የሊቁን የሕይወት ታሪክ እና አበርክቶ የሚያስተዋውቅ ነው።

በዚህ ጥናት ሊቁን በተመለከተ በጎሩይ ወልደ ሥላሴ፣ በአድማሱ ጀምበሬ፣ በክራፕፍ፣ በሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ ዐምደ ጽዮን ተሰማ በትንሣኤ መጽሔት በጻፉት ጽሑፍ እና በሌሎችም ከዘመናችን የደረሱ ቀዳማይ እና ካልኣይ የመረጃ ምንጮችን በመሰብሰብ በጊዜ ቅደም ተከተል መተንተን፣ የተዛነፈ ጉዳይ ሲገጥም ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከድርጊት እና መሰል ጉዳዮች አንጻር ለመመርመር ተሞክሯል። ይህም ማለት ሁነቶችን በማገጣጠም ትክክለኛ የሊቁ ታሪክ ላይ ለመድረስ የተገኘውን መረጃ ቅደም ተከተል አስይዞ የመተረክ፣ የመተንተን እና የመገምገም ተግባራት ተከናውነዋል። የጥናቱ ጠቀሜታ የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ተጠብቆ እንዲኖር ዕድሜ ልካቸውን ሲጋደሉ የኖሩትን ሊቅ ትውልዱ እንዲያውቃቸው፣ አጥኚውም ከበረከታቸው ለመካፈል የተፈጸመ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮም ሆነ በየዘመናቱ የገጠማትን ተጋድሎ በጥልቀት ለማጥናት ለሚፈልጉ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ምሁራን ግብአት ሆኖ ያገለግላል የሚል እምነት አለኝ። አለቃ ምላት የአራቱም ጉባኤ ቤት ሊቅ የነበሩ ቢሆንም Krapf የተባለ ሚሲዮናዊ ሸዋ በገባ ጊዜ በአንድ በኩል እምነቱን ለመረዳት በተደጋጋሚ ይጠይቁታል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ዕብራይስጥ እና መልክአ ምድርን የተመለከተ ትምርህት (Geography) ለመማር ያደርጉት የነበረው ጥረት ለዘመናችን ትውልድ አርአያ የሚሆን ነው። እንዲህ ያለው ተግባር የሊቃወንቱን ዕውቀት በቃኝ አለማለትና ለዕውቀት የነበራቸውን ጉጉት ወይም ጥማት ስለሚያስገነዝብ የሕይወት ታሪካቸውን ለማጥናት ምክንያት ሆኖኛል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የሕይወት ታሪክ ጥናት በውጪው ዓለም ዜና አበው“patrology” ተብሎ ከሚጠራው ጥናት ጋር የሚመሳሰል ነው። ይህን ጥናት ግብፃዊው ቄስ ያዕቆብ ማላቲ (in Tadros, 1993, p.7)

> *In studying Patrology, we face two integral systems: one the scientific system, which the West adopts: Scholars are interested in publishing*

> *the texts of the Patristic literature in a scientific accurate translation to modern languages, criticizing them and studying their doctrines and thoughts: theological, ascetic, spiritual, biblical, etc. two the spiritual system, which the East adopts: The Eastern churches are interested in enjoying the richness of the Fathers' spirituality, by penetrating the depth of the texts and putting them to practice within the church life. These two systems are inseparable, for they are integral. The scientific system helps to establish sound basics, and the spiritual system transfers the texts into life and practice.*

በማለት ገልጦታል። የአማርኛ ትርጉሙም እንደሚከተለው ነው፤

> *ዜና አበው የሚባለው ጥናት ሁለት መሠረታዊ ዘዴዎችን በማሰናሰል የሚከናወን ነው። የመጀመሪያው ምዕራባውያን የሚቀበሉት ሳይንሳዊ ዘዴ ሲሆንሊቃውንት የሃይማኖት አባቶችን ድርሰቶች ትክክለኛ በሆነ ሳይንሳዊ መንገድ የሚያቀርቡበት ነው። ይህም ሂስን የሚጨምር ሲሆን አስተምህሯቸውን፣ የነገረ መለኮት ዕውቀታቸውን፣ ገዳማዊ ሕይወታቸውን፣ መንፈሳዊ ተጋድሏቸውን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜያቸውን የሚመረምሩበት ነው። ሁለተኛው ደግሞ መንፈሳዊ ዘዴ የሚባለው ነው። ይህም ምሥራቃውያን ትኩረት የሚያደርጉት ዘዴ ነው። ምሥራቃውያን አብያተ ክርስቲያናት የሚሳቡት በአባቶች መንፈሳዊ ሕይወት ነው። ድርሰቶቻቸውን በጥልቀት መመርመር ያንን በተግባር መኖር ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ሁለቱም ዘዴዎች ሥርዓቶች የማይነጣጠሉ ናቸው። ምክንያቱም የሳይንሳዊ ዘዴው ጤናማና መሠረታዊ ነገሮችን ለመመርመር ይረዳል። መንፈሳዊ ዘዴው ጽሑፎቹን ሰበሕይወት መለማመድ ይገባል።*

ከያዕቆብ ማላቲ ጽሑፍ መረዳት የሚቻለው "ዜና አበው" የሚባለው ጥናት ሁለት ጉዳዮችን በማጣመር የሚከናወን መሆኑን ነው። እነዚህም ሳይንሳዊ ዘዴ እና መንፈሳዊ ጉዳይ ናቸው። አንባብያን መረዳት የሚገባቸው ማንኛውም የሕይወት ታሪክ ጥናት ሁለቱንም ዘውጎች የማያሟላ ወይም አጣምሮ የማይዝ የሚገባው መሆኑን ነው። የሕይወት ታሪክ በሳይንሳዊ መንገድ የሚጠና ቢሆንም መንፈሳዊው ነገር ይጎድለዋል። ሁለቱም ጉዳዮች በዜና አበው ጥናት የማይነጣጠሉ ሲሆኑ፣ ሁለቱም ነጥቦች እንደአለቃ ምላት ላሉ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን የሕይወት ታሪክ ጥናት አገልግሎት ላይ ይውላሉ።

## ፪. የግለ የሕይወት ታሪክ እንደሥነ ጽሑፍ ዘውግ

የሕይወት ታሪክ አንድ ታዋቂ ግለሰብ በዘመኑ የወጣ የወረደበትን፣ ያለፈ የአገደመበትን አንኳር አንኳር ጉዳይ በመተረክ በአንድ በኩል መልካም ማድረግን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአተራረክ ቴክኒክን ልንማርበት የሚያስችል የጽሑፍ ዘውግ ነው። ይህን አንዳንድ የሥነ ጽሑፍ ተመራማሪዎች (ለምሳሌ Abrams, 1999, p.42) እንዲህ ብለው ይበይኑታል፤

> *ግለ ታሪክ ወይም የሕይወት ታሪክ የግለሰቦች ታሪክ ነው። ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው የፈጸሟቸውን ድርጊቶች፣ ያከናወኗቸውን ኩነቶች፣ ያስታወሷቸውን ክንዋኔዎች፣ ያለፉባቸውን ገጠመኞች፣ የተጓዙባቸውን የሕይወት ጎዳናዎች፣ ከሰዎች፣ ከፈጣሪያቸው፣ ከእንስሳት ወይም ከሌላ ነገር ጋር የመሠረቷቸውን ግንኙነቶች የሚተርኩበት የሥነ ጽሑፍ ዘውግ ነው።*

Cuddon (1977) እና ሣህለ ሥላሴ (፲፱፻፺፱) የ Abrams ን ሐሳብ፣ ይጋሩታል። አስቀድሞ ከተጠቀሰው ጽሑፍየምንረዳው ግለታሪክም ሆነ የሕይወት ታሪክ የግለሰቦች ታሪክ መሆኑን፣ ግለሰቦች በሕይወት ዘመናቸው ያጋጠሟቸውን ሁነቶች የሚተርኩበት የጽሑፍ ዘውግ መሆኑን ነው። ግኡዝ ከሆነው ዓለም ጋር ብቻ ሳይሆን ከረቀቀው ዓለም ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ተርከው በአንድ በኩል ስሜታቸውን የሚገልጡበት፣ እግረ መንገዳቸውን ደግሞ ሌሎችን ከሕይወታቸው የሚስተምሩበት መሆኑን ያስረዳል። በሌላ በኩል ደግሞ "በሕይወት ታሪክ እና በግለ ታሪክ መካከል ያለው ልዩነት የተራኪው ማንነትና ሚና ብቻ ነው። ተራኪው የታሪኩ ባለቤት ከሆነ ድርሰቱ "ግለ ታሪክ" ሲባል፣ ተራኪው የታሪኩ ባለቤት ሳይሆን፣ የሌላ ሰውን የሕይወት ታሪክ የሚተርክ ከሆነ ደግሞ "የሕይወት ታሪክ" እንደሚባል ጸሐፍያን ገልጠዋል (Abrams, 1999, pp.42-43፤ ሣህለ ሥላሴ ፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፷፪)። ይህ ብይን የግለሰቦች ታሪክ ስያሜ የሚለያየው በሚጽፉት ግለሰቦች ማንነት ላይ መሆኑን ያስገነዝባል። እንዲህ ያለው የሥነ ጽሑፍ ዘውግ በተቃራኒ የሚቆሙ ሁለት ዐበይት ባሕርያት አሉት።የመጀመሪያው በአዎንታዊነቱ የሚጠቀስ ሲሆን መረጃን ወይም ዕውቀትን ከምንጪ እንዲገኝ ማስቻሉ ነው።

በ Cuddon (1977) ገለፃ መሠረት፣ ፀሐፊው የራሱን ታሪክ "እኔ" እያለ በሕይወቱ ያጋጠመውን፣ የደረሰበትንና የደረሰለትን፣ ያሳዘነውንና ያስደሰተውን፣ ተስፋ ያስቆረጠውና ተስፋ የፈነጠቀበትን፣ በጥቅሉ ስሜቱን፣ ዐሳቡን፣ ምኞቱን፣ ፍልስፍናውን ስለሚነግረን በእምነት እናዳምጠዋለን። እዩልኝ የሚለውንም በእምነት እናይለታለን። ቀድሞ ነገር ከራሱ በላይ ስለእርሱ ማን ሊነግረን ይችላል? ሁለተኛው

ደግሞ በአሉታዊ ሊጠቀስ የሚችለው ጉዳይ ነው። Abrams (1999) እንደሚሉት፣ ግለ ታሪክ በባሕርዩ ግለሰባዊነት ስለሚያጠቃው፣ ባለታሪኩ ራሱን ያለቅጥ ከፍ በማድረግ ሌሎች ሰዎች በታሪክና በማኅበራዊ ሕይወት ያላቸውን ድርሻ ያላግባብ ሊቀማ መቻሉ ነው። "ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ" እንደሚባለው፣ የታሪኩባለቤት በዘመኑ ተፈጸመ ያለውን ሁሉ እንደተደረገበት ሁኔታ ሳይቀንስ ወይም ሳይጨምር ያቀርባል ማለት በራሱ ጥያቄ የሚያስነሣ ጉዳይ ነው።

የግለ ታሪክ የመረጃ ምንጭ የራሱን ታሪክ የሚጽፈው ግለሰብ ትውስታ በመሆኑ ከዕውቀት፣ ከመረጃ እጥረት ወይም ውስንነት ወይም አንድን ሁነት ለመግለጽ ፈቃደኛ ባለመሆን ማለፍ፣ ወይም አዛብቶ ማቅረብ ሊከሠት ይችላል። ይህ ድርጊት ታሪክን በአዲስ ቅርጽና መንገድ እንደ ገና እንዲተረክ መንገድ ስለሚከፍት አንባቢያን በነገሩ፣ በጉዳዩ ወይም በክሥተቱ ላይ የተሳሳተ አስተያየትና ግምት እንዲይዙ ያደርጋል። ይህም የተራኪውን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባዋል። በዚህ ሂደት ሊፈጠር የሚችል ስሕተት ከሚታረምባቸው መንገዶች አንዱ የጻፉትን ታሪክ መልሶ በመመርመር ማርታት ነው። ከዚህ ብይንም ይባል ስጋት በመነሣት የአለቃ ምላት ሀብቴን የሕይወት ታሪክ ስንመረምረው ታሪካቸው ሳይጻፍ ቀርቶ ከዘመናችን ያለመድረስ ተግዳሮት እንደ ገጠመው መረዳት ይገባል። መታወቅ የሚኖርበት የሊቁን ታሪክ ማጥናት ያስፈለገው ያልሠሩትን የሠሩ ለማስመሰል፣ ያለስማቸው ስም ለመስጠት ሳይሆን ከዘመናችን የደረሰውንም ቢሆን ማጥናት አስፈላጊ በመሆኑ ነው። አስፈላጊነቱም ታሪካቸው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል በመሆኑ ነው።

## ፫. አለቃ ምላት ማን ናቸው?

አለቃ ምላት የተወለዱት በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ሞረት አቡነ ዜና ማርቆስ ነው። አለቃ ለማ ኃይሉ በበኩላቸው የሊቁን የትውልድ አካባቢ መራ ቤቴ ወግዳ ከሚባል ቦታ ያደርጉታል (መንግሥቱ፣ ፲፱፻፶፱)። አባታቸው ሀብቴ ይባላሉ። ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ሊቁ የተወለዱበትን ቦታ ሞረት አቡነ ዜና ማርቆስ (፲፱፻፹፩፣ ገጽ ፪፻፴) መሆኑን ቢነግሩንም በሌላ በኩል ደግሞ የሊቁ አባት የመኖሪያ አካባቢ አንኮበር መሆኑን ሥርግው (፲፱፻፹፩፣ ገጽ ፲፩) "ሀብቴ በ፲፱ኛው ምእት የነበረ የአንኮበር ሰው፣ በግብርና ሥራ ተሰማርቶ የሚኖር፣ አንድ ወንድ ልጅ ባስወለደ ጊዜ ፶ በጎች፣ ፶ ፍየሎች፣ ፶ ባዝራዎች ወልደው አደሩ ይባላል። ስለዚህ የልጁን ስም ምላት አለው። ይኸውም ልጅ አለቃ ምላት በመባል የታወቁት የሸዋ ሊቅ ናቸው" በማለት ይናገራሉ። ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ከገለጧቸው ሁለት የሊቁ የትውልድ ቦታዎች የአንዱን ማስተካከል የነበረባቸው መሆኑ የሚገለጠውም ለዚህ ነው። የምላት ሀብቴን ታሪክ በእግረ መንገድ ከጻፉ ሰዎች መረዳት የሚቻለው ግን አለቃ ምላት

ሞረት አቡነ ዜና ማርቆስ አካባቢ ተወልደው አንኮበር ጊዮርጊስ መማራቸው ነው። ከዘመናት በኋላ ከአንኮበር ሲሰደዱም የሄዱት ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ወደ ሞረት አቡነ ዜና ማርቆስ መሆኑን መረዳት ይገባል።  ምላት ሀብቴ በተወለዱ ጊዜ ከእያንዳንዱ እንስሳ የተወለዱትን ግልገሎች ቁጥር ኀሩይ ወልደ ሥላሴ ሰባት፣ ሰባት ያደርጉታል (ኀሩይ፣ ፲፱፻፲፫፣ ገጽ ፲፫)። መታወቅ የሚኖርበት ዋናው ቁም ነገር ግን ብዙ ክበድ የነበሩ የወላጆቻቸው የቤት እንስሳት ምላት በተወለዱበት ዕለት በመውለዳቸው ምክንያት ሲጠሩበት ለኖሩት ስያሜ ምክንያት መሆኑ ነው። በአንድ ቀን ብዙ የቤት እንስሳት መውለዳቸው ብቻ ሳይሆን የተወለዱት እንስሳት ቁጥር ተመሳሳይ መሆኑ ለስያሜው ምክንያት ሆኗል ማለትም ይቻላል።  ምላት ሀብቴ ሊወለዱ የሚችሉት በ፲፰ኛው መቶ መጨረሻ ወይም በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው።

አለቃ ዐምደ ጽዮን ተሰማ "የተወለዱትም በ፲፰፻፰፪ ዓ.ም ዋቅሹም ኀበዜ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው ተሾመው በነበረበት ዘመን ነው (ትንሣኤ መጽሔት፣ ቍጥር ፺፣ ኅዳር ፲፱፻፸፬፣ ገጽ ፲) በማለት የጻፉት ትክክል አይደለም። የአለቃ ዐምደ ጽዮንን ዐሳብ ከተቀበልን አለቃ ምላት በዚህ ዓለም የኖሩት ከሃያ ዓመት ያልበለጠ ዘመን መሆኑን መቀበል አለብን። ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ምላት ሀብቴ የተወለዱበትን ዘመን በ፲፱ኛው ምእት መጀመሪያ (፲፱፻፰፱፣ ገጽ ፪፻፴፪) ያደርጉታል። ምላት ሀብቴ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የሆነውን ንባብ፣ ውዳሴ ማርያምንና መዝሙረ ዳዊትን የተማሩት በተወለዱበት ሞረት አቡነ ዜና ማርቆስ አካባቢ በሚገኝ ደብር ነው። በ፲፰፻፴፬ ዓ.ም. በንጉሥ ሣህል ሥላሴ ዐዋጅ አንኮበርን ለቀው እንዲወጡ የተደረጉት ከአለቅነታቸውና ወንበር ዘርግተው ከሚያስተምሩበት መሆኑን በዘመኑ የዓይን እማኝ የነበረው ክራፕፍ የጻፈው የሚያመለክተውን በሚገባ ከመረመርነው ግን ሊቁ ሊወለዱ የሚችሉት በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ሳይሆን በ፲፰ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ ይሆናል። የሥርግው ዐሳብ ወደ እውነቱ የሚጠጋው በስደቱ ዘመን ገና ተማሪ ከነበሩ ብቻ ነው። ይህ አለመሆኑን ደግሞ ክራፕፍ ነግሮናል። ኀሩይ ወልደ ሥላሴ እንደሚሉት ምላት ሀብቴ "እጅግ የተማሩ ሊቅ ነበሩ"።

አድማሱ ጀምበሬ የጻፉት "ምላት ሀብቴ አንኮበር ሚካኤል ወንበር ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት የአራቱ ጉባኤ ሊቅ ከአለቃ ወልደ ሐና ዘንድ ሔደው መማር ሲጀምሩ ባለጸጋ የነበሩት አባታቸው ስንቃቸውን ማር እያስጫኑላቸው ጠጅ እየጠጡ ተምረው የአራቱ ጉባኤያት መምህር (አድማሱ፣፲፱፻፰፫ ዓ.ም፣ ፪፻፲፫) መሆናቸውን ነው። ሊሆን

የሚችለው ግን አንኮበር ሚካኤል ሳይሆን ጊዮርጊስ ነው። ምክንያቱም መምህራቸው የአንኮበር ጊዮርጊስ አለቃ ነበሩና። አለቃ ምላት የመጻሕፍተ ሐዲሳትን ትርጓሜ በመማር ላይ በነበሩበት ጊዜ ከመጻሕፍተ ብሉያት ተማሪዎችም ጋር ይከታተሉ ስለነበር እና መጻሕፍተ ሊቃውንትን በሚማሩበት ጊዜ ከመጻሕፍተ መነኰሳት ደቀ መዛሙርት ጋር መጻሕፍተ መነኰሳትን ያጠኑ ስለነበር አራቱን ጉባኤያት ለማወቅ ብዙ ዓመታት አልወሰደባቸውም (ትንሣኤ መጽሔት፣ ፲፱፻፸፬፣ ገጽ ፲)። ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (፲፱፻፷፱፣ ገጽ ፩፻፴፭) የጻፉት በተወሰነ መልኩም ቢሆን ከአድማሱ ጀምበሬ ዐሳብ የሚለይ ሲሆን ዐሳባቸውን፤

> *ምላት ሀብቱ ሲማሩም እንደ ሌሎቹ ተማሪዎች እየለመኑ ቆሎ እየቆረጠሙ ሳይሆን በጌትነት የሚፈልጉትን እየተመገቡ ነበር። የሊቁ አለቃ ምላት ሀብቱ ዋና ትምህርታቸው መጻሕፍተ ሐዲሳት ቢሆንም ፍትሐ ነገሥት እና መጻሕፍተ ብሉያትንም ተምረዋል። ሊቁ በጣም ቅኔ ዐዋቂ በመሆናቸው በሊቅነታቸውና በሚቀኙት ቅኔ በየጊዜው በሊቃውንት ይደነቁ ነበር። አለቃ ምላት ይከበሩ እና ይደነቁ የነበረው በሊቅነታቸው ብቻ ሳይሆን ነውር በሌለበት ድንግልናዊ ሕይወታቸው ጭምር ነበር።*

በማለት ገልጠዋል። የሥርግው ሐብለ ሥላሴ ጽሑፍ አለቃ ምላት ሙሉ የአራቱም ጉባኤ ሊቅ መሆናቸውን ባይገልጥም አድማሱ ጀምበሬ ግን የአራቱም ጉባኤ ሊቅ እንደ ነበሩ ጽፈዋል። አለቃ ለማም የአለቃ ምላትን ሊቅነት ደጋግመው መስክረዋል። መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ትዝታየ በተሰኘው መጽሐፋቸው አለቃ ምላት በአንኮበር ወንበር ዘርግተው ፍትሐ ነገሥትን ያስተምሩ ስለነበር አለቃ ወልደ ያሬድን ፍትሐ ነገሥት እንዳስተማሯቸው ጽፈዋል (፳፻፪፣ ገጽ ፺)። ይህን ዐሳብ አለቃ ለማ ኃይሉም ያጠናክሩታል (መንግሥቱ ፣ ፲፱፻፶፱፣ ገጽ ፻፳፩)። አለቃ ዐምደ ጽዮን ተሰማ አለቃ ምላት ሀብቱ የተማሩበትን ቦታ በድፍን አንኮበር በማለት ቢጽፉም አድባራቱ አልተገለጡም። ሊማሩ የሚችሉት ግን አንኮበር ቅዱስ ጊዮርጊስ ወይም አንኮበር ሚካኤል ነው። መምህራቸው ወልደ ሐና እልቅና ከመሾማቸውበፊት ወንበር ዘርግተው ያስተምሩበት ከነበረ ደብር መማራቸውን መረዳት ተገቢ ነው። ይህም አንኮበር ጊዮርጊስ ነው። በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በተተከለው አንኮበር መድኃኔ ዓለም ዘመን እስከሚለወጥባቸው ድረስ ገንነው ወንበር ዘርግተው ሲያስተምሩ የኖሩት ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ ብለው ያምኑ የነበሩ ሊቃውንት ናቸው። በተዋሕዶ ከበረ ብለው ያምኑ የነበሩት ሊቃውንት አንኮበር ጊዮርጊስ እና አንኮበር ሚካኤል የነበሩ ቢሆንም በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የመሳደድ ዕጣ ደርሶባቸው ነበር።

ኀሩይ ወልደ ሥላሴ (፲፱፻፲፰፣ ገጽ ፲፰) ስለ አለቃ ምላት፤

> *…በደግነትና በጌትነት እጅግ ስመ ጥሩ ነበሩ። ከጌትነታቸው የተነሣ 'ከጠጅ በቀር ጠላ የጠጣሁ እንደ ሆነ ጉንፋን ይይዘኛል' ይሉ ነበር ይባላል። ደግሞም ለልብሳቸው ንጹሕነት እጅግ ይጠነቀቁ ነበርና ዝንብ በልብሳቸው ላይ ዐርፋ የተመለከቱ እንደ ሆነ ይቺ ዝንብ በልብሴ ላይ ያረፈችው እድፍ ብታገኝበት ነው ብለው በቶሎ ወደ አጣቢ ይሰዱት ነበር ይባላል። ሊቁ በቤተ መንግሥትም በጣም የታወቁ ስለነበሩ ከመዓርጋቸው ሳይወርዱ ዐረፉ።*

በማለት ታሪካቸውን በአጭሩ ጽፈዋል። እንዲህ ዓይነት ምቾት የማያሸንፈው ንጽሕና የሚገኘው በጽኑ ተጋድሎ ነው። ሁሉ ነገር ሞልቶ ራስን በንጽሕና ደንግለው ኖረው ለዘለዓለማዊ ክብር የሚበቁ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ሕይወት የሚያስቀና ብቻ ሳይሆን የሚያስገርምም ጭምር ነው። አለቃ ለማ ኃይሉ (በመንግሥቱ ውስጥ፣ ፲፱፻፶፱፣ ገጽ ፻፳፩-፻፳፪) ስለ ሊቁ አለቃ ምላት ሲተርኩ ከአድናቆት ጋር ነው።

> *በዘመኑ አንኮበር ሚካኤል የነበረው ተማሪ ተከፋፍሎ መጻሕፍተ ብሉያት እና መጻሕፍተ ሐዲሳት ይማር የነበረው ከአለቃ ምላት ዘንድ እየተመገበ ነበር። አለቃ ምላት ተቀምጠው ግብር ይገባል። ከጓዳ መኝታ ክፍል አለቻቸው ጥቂት እንቅልፍ ሸለብ ካደረጉ በኋላ ተነሥተው በጸሎት ቆመው ያድራሉ። የእነ አለቃ ወልደ ያሬድ ሁሉ አሳዳጊ እርሳቸው ነበሩ። ብሉያት፣ ሐዲሳት እና ፍትሐ ነገሥት የተማሩ ሊቅ ሲሆኑ ትውልዳቸው መራቤቴ ወግዳ ነው። ቆለኛ ሲሆኑ ፍጹም ሸዬ (የሸዋ ሰው ለማለት ነው) ናቸው። ድንግልናቸው ሌላ ነው። አለቃ ምላትን ቀና ብላ በዓይኗ የምታይ ሴት አልነበረችም።*

በማለት በሸዋ እጅግ የተከበሩ እንደ ነበሩ ሲነግሩን እንኳን እርሳቸው በዝና ብቻ የምናውቃቸው ከዘመናቸው ያልደረስን ክርስቲያኖች በድንግልናቸው ንጽሕና መንፈሳዊ ቅንዓት ያድርብናል።

## ፬. አለቃ ምላትና አንኮበር

አለቃ ምላት "በቤተ መንግሥትም የታወቁ ስለነበሩ ከመዓርጋቸው ሳይወርዱ ዐረፉ" የሚለውን የጎሩይን ዐሳብ ለመቀበል የሚያስቸግረው ሊቁ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ ብለው የሚያምኑ በመሆናቸው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በጥቅምት ወር ፲፰፻፴፬ ዓ.ም. አውጥተውት በነበረው ዐዋጅ ምክንያት አንኮበርን ለቀው እንዲወጡ ተደርገው እንደ ነበር የሚተርከውን የጀርመናዊውን ፕሮቴስታንት፣ የ Krapf ን (1860, p. 40)፣ የሥርግው ሐብለ ሥላሴን እና የአድማሱ ጀምበሬን ጽሑፍ ስናነብ ነው (አድማሱ፣ ፲፱፻፰፫፣ ገጽ ፪፻፲፫)። በተጠቀሰው ዘመን ምላት ሀብቴ አለቃ እንደ ነበሩ የምንረዳው ክራፕፍ አለቃ እያለ ስለሚጠራቸው እና ከአለቅነታቸው መሻራቸውን ስለነገረን ነው። ለሃይማኖታቸው ባላቸው አቋም በቦታው ከነበሩ የተዋሕዶ ሊቃውንት ቀዳሚው እንደ ነበሩ የሚገልጠውም እነ አለቃ ወልደ ሐና ከእልቅና ሳይሻሩ እርሳቸው ተሽረው ካለሥራ እንዲቀመጡ መደረጋቸውን Krapf ስለሚናገር ነው። Krapf በምሥራቅ አፍሪካ የነበረውን የሚሲዮናዊነት ቆይታ በተመለከተ ካሳተመው የጉዞ ማስታወሻ መጽሐፉ መረዳት የሚቻለው ከተጠቀሰው ዘመን አስቀድሞ አለቃ ወልደ ማርያም ካረፉ በኋላ አለቃ ምላት በአንኮበር ከተማ በሚገኘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ወይም Krapf አንኮበር በገባበት ዘመን አለቃ ተሾሞለት እንደነበር ላልተገለጠው አንኮበር ሚካኤል ዕልቅና ተሾመው እንደነበር ፍንጭ የሚሰጥ መረጃ ትተውልን ያለፉ መሆኑን ነው። ለአለቃ ምላት እና ለአለቃ ወልደ ሐና የተለየ ቀረቤታ የነበረው Krapf (1860, p.86):

> *"August 1 1839 since I was in the Church of st. George several priests have visited us to talk about religious subjects. Indeed, most of the persons who have come to us for that purpose are of that Church, the reason of which may be, that half a year ago, Alaca Milat was dismissed by the king in consequence of the disputes about the second and third births of Christ. The people st. George believe in two births"*

*በማለት ጽፏል።*

> *ትርጉሙም ሐምሌ 25 ቀን* 1831 ዓመተ ምሕረት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በነበርኩበት ወቅት በርካታ ካህናት ስለሃይማኖታዊ ጉዳይ ለመነጋገር ወደእኛ መጡ። ወደእኛ የመጡት አብዛኞቹ የዚያው ቤተ ክርስቲያን ካህናት የሆነበት ምክንያት በሸዋው ንጉሥ በሣህለ ሥላሴ ከመንፈቅ በፊት አለቃ ምላት የክርስቶስ ልደት ሁለት ነው በሚሉ

ተዋሕዶዎች እና ሦስትልደት ነው በሚሉ ጸጎች መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ ስለነበር ሊሆን ይችላል። የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ክርስቲያን ክርስቶስ ሁለት ልደት አለው ብሎ ያምን ነበር ብሏል።

Krapf ሐምሌ ፳፰ ቀን ፲፰፻፴፩ ዓመተ ምሕረት በጻፈው የዕለት ማስታወሻ ዘገባው አለቃ ምላት ከስድስት ወር በፊት ከአንኮበር ጊዮርጊስ ወይም ከአንኮበር ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አለቅነት ተሽረዋል። ነሐሴ ፳ ቀን ፲፰፻፴፩ ዓመተ ምሕረት ክራፕፍ አለቃ ወልደ ሐና ወንበር ዘርግተው ያስተምሩበት እና እልቅና ተሾመውበት ወደ ነበረው አንኮበር ጊዮርጊስ በሔደ ጊዜ አለቃ ወልደ ሐና እና አለቃ ምላት የቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅን መጽሐፍ እየተረጎሙ እንዳገኛቸው ጽፏል። እርሱ እንዲህ ይበል እንጂ ሊሆን የሚችለው ጎልማሳው አለቃ ምላት የግእዙን ዘር እያነበቡላቸው፣ አረጋዊው አለቃ ወልደ ሐና ደግሞ በአንድምታ እየተረጎሙ ሊያገኛቸው መቻሉ ነው። ሁለቱ ሊቃውንት በዕለቱ Krapf ን የጠየቁት ታሪካቸው በመጽሐፈ ኩፋሌ ተጽፎ ስለሚገኘው ብሔሞት እና ሌዋታን የእርሱ አመለካከት ምን እንደሆነ እንዲነግራቸው ነበር። Krapf አንኮበር ከመድረሱ ከስድስት ወር አስቀድሞ ምላት ሀብቴ ከደብር አለቅነታቸው እና ከጉባኤ ቤት መምህርነታቸው በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ተሽረው እንደ ነበር Krapf ጽፏል። አለቃ ምላት በዘመኑ ጎልማሳ ስለነበሩ እና ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ ብለው በሚያምኑመምህራን ዘንድ ይፈሩ ስለነበር ንጉሡ በተጽዕኖ ማንሣታቸውን ፍንጭ የምናገኘው ከአለቃ ለማ ኃይሉ ትዝታ ነው።

ጸጎች ሊቁን ንጉሡ እንዲያነሡላቸው አስደርገው ተዋሕዶዎች ብቻ ይገኙበት ከነበረው ቤተ ክርስቲያን ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ ብሎ የሚያምን መምህር መላክ ሊያስከትለው የሚችለውን ችግር ንጉሡ ተረድተው ብዙም ተጽዕኖ የማይፈጥሩትን፣ ዕድሜያቸው በመግፋቱ ምክንያት በተደጋጋሚ ይታመሙ እንደነበር ክራፕፍ የሚነግረንን አረጋዊውን ሊቅ ወልደ ሐናን ሾሞ ሊሆንም ይችላል። አለቃ ምላት ካለሥራ በመቀመጣቸው እና በዘመኑ አለቅነት ወንበር ዘርግቶ ማስተማርንም ይጨምር ስለነበር እልቅናውን ስለተሻሩ ከመምህራቸው ዘንድ ከመጻሕፍተ ሊቃውንት አንዱ የሆነውን የሊቁን የዮሐንስ አፈ ወርቅን ድርሳን እና ተግሣጽ እየተማሩ፣ አስቀድመው ተምረውት ከነበረም እየደገሙት ነበር ማለት ነው (Krapf, *1860, p.101*)። ከክራፕፍ ገለጣ የምንረዳው ሌላው ነገር በተጠቀሰው ዘመን አለቃ ምላት ከእልቅና ቢሻሩም በከተማው ለመኖር አለመከልከላቸውን ወይም አለመሰደዳቸውን ነው።

Krapf ከሚኖርበት ቤት በጠዋት ተነሥቶ ወደ አንኮበር ጊዮርጊስ በሄደበት ወቅት ከስድስት ወር በፊት ተሽረው የነበሩትን አለቃ ምላትን ማግኘቱን ቢነግረንም በትክክል ከየትኛው ደብር እልቅና እንደተሻሩ አልገለጠም። ታሪኩን የጻፈው አንኮበር ጊዮርጊስ ባለበት ሰዓት በመሆኑ የተሻሩት ከአንኮበር ጊዮርጊስ ነው ሊያሰኝ ቢችልም ይህን ማጠቃለያአምኖ ለመቀበል ሁለት ተግዳሮት ይገጥማል። የመጀመሪያው በዘመኑ ወልደ ሐና የደብሩ አለቃ ስለነበሩ፣ እርሳቸውም እልቅናውን ከማን ቀጥለው እንደተረከቡት አለመታወቁ ነው። ሌላው ተግዳሮት ደግሞ በአካባቢው የሚገኙትን አድባራት በዘመኑ ያስተዳድሯቸው የነበሩ አለቆች በክራፕፍም፣ በሥርግው ሐብለ ሥላሴም ሲዘረዘሩ ተዋሕዶዎች ብቻ ያገለግሉበት የነበረው ሁለተኛው ደብር የአንኮበር ሚካኤል አለቃ አለመጠቀሱ ምላት ሀብቴ ከእርሱ ተነሥተው ይሆናል የሚል ግምት ስለሚያሰጥ ነው። Krapf እንደጠቀሰው፣ አለቃ ለማ ኃይሉም እንደሚጋሩት ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ተዋሕዶዎችን አለቃ ምላትን፣ አለቃ ወልደ ሐናን፣ ኪዳነ ወልድ ኤዎስጣቴዎስን እና ሌሎችንም ከአንኮበር ያስወጧቸው ነውጠኛ እና አክራሪ በነበሩ የሦስት ልደት ተከታዮች ግፊት ነው። ንጉሡ የተዋሕዶ ሊቃውንትን ከአንኮበር አስወጥተዋቸው የነበረ ቢሆንም ከጥቅት ጊዜ በኋላ ለአለቃ ምላትእንዶዴ ተክለ ሃይማኖት በሚባል ከአንኮበር ወደ ቆላው ከሚገኝ ደብር ማደሪያ መስጠታቸውየተዋሕዶ ሊቃውንትን ያባረሯቸው በጾጎች ተጽዕኖ እንጂ እርሳቸው ክፉ ስለነበሩ ላለመሆኑ ፍንጭ ይሰጣል። በዘመኑ ማደሪያ መስጠት ማለት እልቅና መስጠት በመሆኑ በቦታው ወንበር ዘርግተው አስተምረው ሊሆን ይችላል።

በዚያ ዘመን አለቃ ምላት ሀብቴ የአንኮበር ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አለቃ ነበሩ ብሎ መገመት የሚቻለው Krapf አንኮበር ከመድረሱ ከስድስት ወር በፊት ከአለቅነት የተነሡት ከአንኮበር ጊዮርጊስ የሚመስል ፍንጭ ከክራፕፍ የጉዞ ማስታወሻ ስለምናነብ ነው። የአንኮበር ጊዮርጊስ አለቃ የነበሩት መምህር ወልደ ማርያም እንደ ሞቱ ወዲያው የተተኩት አለቃ ወልደ ሐና ከሆኑ አለቃ ምላት የአንኮበር ሚካኤል አለቃ ሆነው ቆይተው Krapf ከጠቀሰው ዘመን ስድስት ወር አስቀድሞ ተሽረዋል ማለት ነው። ምላት ሀብቴ ከአለቃ ወልደ ሐና አስቀድሞ የአንኮበር ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንን እልቅና ተሹመው ሊሆን እንደሚችል ከክራፕፍ ጽሑፍ መገመት ቢቻልም በዘመኑ አለቃ ያልነበረው የአንኮበር ሚካኤል አለቃ ነበሩ የሚለው ያሳምናል። ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ምላት ሀብቴን አለቃ አድርጎ የሾማቸው እንደ ክራፕፍ ገለጣ በ፬ሥራ ሁለት ዓመቱ፣ እንደ ኀሩይ ወልደ ሥላሴ ደግሞ በ፲፰ ዓመቱ የነገሠው Krapf ሸዋ በነበረበት ዘመን ከነገሠ ሃያ ሰባት ዓመት ሆኖት የነበረው የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ነው (Krapf, 1860, p. 87)። ሥርግው ሐብለ

ሥላሴ (ዓመተ ምሕረት ያልተጠቀሰ፣ ገጽ ፻፸፩) ዳግማዊ ምኒልክ የአዲሱ ሥልጣኔ መሥራች በተሰኘ መጽሐፋቸው የገለጡት፡-

*ምላት (መምህር) የሊቃውንት መምህር። በእምነቱ የሁለት ልደት ወገን። በሣህለ ሥላሴ ዘመን ሁለት ልደቶች ሲሰደዱ መምህር ምላት አልተሰደደም። በትምህርቱም ላይ ፈሊጥ ዐዋቂ ስለነበረ ምክር ይዋጣለት ነበረ። ወደ ፊት እንደምንገልጠው ዐፄ ዮሐንስን እና ንጉሥ ምኒልክን ካስማሙት ሊቃውንት አንዱ ነበረ። በዚህም ላይ ንጽሕናን የሚጠብቅ ጥሩ ኑሮ የሚኖር ነበር። አቡነ ማቴዎስ በ፲፰፻፸፫ ዓመተ ምሕረት ሸዋ ሲደርስ በንጽሕናው እና በድሎቱ አለቃ ምላት ቤት የተሻለ በመሆኑ ያረፈው እዚያ ነበር። የእንግድነቱ ወራት አልፎ አለቃ ምላት ቤቱን እንዲለቅለት ጳጳሱን ቢጠይቀው ከዚያ የተሻለ ቤት እንደማያገኝ ስለዐወቀ እምቢ አለ። አለቃ ምላት ለዳግማዊ ምኒልክ ቢያመለክት ሌላ ቤት እና ቦታ ሰጠው እንጂ የቀድሞ ቤቱን አልመለሰለትም*

የሚል ነው። ከሥርግው ገለጣ መስተካከል ከሚኖርባቸው ነጥቦች አንዱ በዘመኑ የዓይን እማኝ የነበረው ክራፕፍ የአለቃ ምላትን አስቀድሞ ከእልቅና መሻር ከሦስት ዓመት በኋላም ከአንኮበር መሳደድ ስለነገረን ነው። ራሳቸው ሥርግውም በተጠቀሰው መጽሐፋቸው "አለቃ ምላት በእምነቱ ምክንያት በሣህለ ሥላሴ ዘመን ከሹመቱ የተሻረ ነበር" (ሥርግው፣ ገጽ 171) ብለዋል። ሥርግው ሁለት ተቃራኒ ዐሳብ በማስፈራቸው ከሁለቱ አንደኛውን ማስተካከል ነበረባቸው። ሥርግው አለቃ ምላት በሣህለ ሥላሴ ዘመን ከሹመቱ ተሻረ በማለት የገለጡት ሌላ ፍንጭ ይሰጠናል። በአንድ በኩል ክራፕፍ ለገለጠው ማረጋገጫ ሲሆን ሊቁ ቅኔንና ትርጓሜ መጻሕፍትን ተምረው አጠናቀው እልቅና መሾማቸው ዕድሜያቸውም ጎልማሳነት ደረጃ የደረሰ መሆኑን ያሳያል።

ዘመኑ ዕውቅና ይሰጥ የነበረው ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ ለሚሉ ሊቃውንት ቢሆንም አለቃ ምላት በሃይማኖታቸው የማያወላውሉ ቢሆኑም እንኳ መሾማቸው ንጉሡ ያከብሯቸው እንደነበር ያስገነዝባል። አለቃ ምላት ተፈርተውና ተከብረው መኖራቸው የታወቀ ቢሆንም በአንኮበር ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ በማለት ያምኑ የነበሩ ሊቃውንት ገንነውና በዝተው በነበረበት ዘመን ሊቁም በማያወላውል አቋማቸው ምክንያት የመሰደድን ጽዋ ቀምሰዋል። በዘመኑ በእርሳቸው ብቻ ሳይሆን በመምህራቸው እና በሌሎች ሊቃውንት የተፈጸመውን ድርጊት Krapf (1860, p.34) የገለጠው፤

*"Although in the year 1840 a royal ordinance had deposed all priests who did not believe in the three births, yet it was only on the 24th November, 1841, that the victorious party was able to put the ordinance in execusion against its rivals. Amid song and Acclamation, the zealots rushed in to the Churches and purified them from the presence of the heretics, among whom were many upright men, such as Alaca melat, Wolda Hana, and others, with whom I had been on the friendliest footing. The victories party pressed for a more rigid veneration of the virigin Mary and of the Saints*

*በማለት ነው። ትርጉሙም እንደሚከተለው ነው፤*

> *ምንም እንኳን በ1832 ዓመተ ምሕረት የንጉሣዊ አገዛዝ ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ ብለው የማያምኑትን የተዋሕዶ ሊቃውንት (ካህናት) በሙሉ ከቤተ ክርስቲያን አለቃነታቸው የሻራቸው ቢሆን ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ ብሎ የሚያምነው አሸናፊው ቡድን በተቀናቃኞቹ ላይ አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ የቻለው ግን ጥቅምት 14 1834 ዓመተ ምሕረት ነበር። ጸጎቹ በዝማሬ እና በመንፈሳዊ ቅንዓት ወደ አብያተ ክርስቲያናት ገብተው እነርሱ መናፍቃን ከሚሏቸው አብያተ ክርስትያናትን ነፃ አደረጓቸው። ከቤተ ክርስቲያን ከተሳደዱት መካከል ብዙ ከእኔ ጋር ወዳጅነት መሥርተው የነበሩት አለቃ ምላት፣ አለቃ ወልደ ሐና እና ሌሎችም ቅን ሰዎች ነበሩ። አሸናፊው ቡድን ለድንግል ማርያም እና ለቅዱሳን ግትር የሆነ አምልኮውን የበለጠ አጠናክሮ ገፋበት።*

Krapf ከገለጠው መስተካከል የሚኖርበት ጸጎች ድንግል ማርያምን እና ቅዱሳንን ማምለካቸውን የበለጠ አጠናክረው ገፋበት የሚለው ነው። Krapf ኦርቶዶክሳውያን ድንግል ማርያምንና ቅዱሳንን የሚያመልኩ አስመስሎ የገለጠው ተዋሕዶዎች ለቅዱሳን የሚሰጡትን ክብር እና አማላጅ ማለታቸውን ለክርስቶስ የሚገባውን አምልኮ ለቅድስት ድንግል ማርያም እና ለቅዱሳን እንደመስጠት ስለሚቆጥረው ነው። አለቃ ምላት "በቤተ መንግሥትም በጣም የታወቁ ስለነበሩ ከመዓርጋቸው ሳይወርዱ ዐረፉ" የሚለውን የጎኑይን ዐሳብ ለመቀበል የሚያስቸግረው ሊቁ ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ ብለው የሚያምኑ በመሆናቸው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በጥቅምት ወር ፲፰፻፴፬ ዓ.ም. አውጥተውት በነበረው ዐዋጅ ምክንያት አንኮበርን ለቀው

እንዲወጡ ተደርገው እንደ ነበር የሚተርከውን የጀርመናዊውን ፕሮቴስታንት የ Krapf ን (1860, p.40)፣ የሥርግው ሐብለ ሥላሴን እና የአድማሱ ጀምበሬን ጽሑፍ ስናነብ ነው (አድማሱ፣ ፲፱፻፰፫፣ ገጽ ፪፻፲፫)። በተጠቀሰው ዘመን ምላት ሀብቴ አለቃ እንደነበሩ በሃይማኖታቸው ታዋቂ ብቻ ሳይሆን ጽኑ አቋም ከነበራቸው የተዋሕዶ እምነት ሊቃውንት ቀዳሚው እንደነበሩ ክራፐፍ ጨምሮ ጽፏል። ተፈርተውና ተከብረው መኖራቸው የተገለጠውም በአንኮበር ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ በማለት ያምኑ የነበሩ ሊቃውንት ገንነውና በዝተው በነበረበት ዘመን ሊቁም በማያወላውል አቋማቸው ምክንያት ለጥቂት ጊዜ የመሰደድን ጽዋ ቢቀምሱም ለረጅም ዘመን በተለይም ዳግማዊ ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ በነበሩበት ዘመን ተከብረው መኖራቸው እውነት ነው።

በዚያ ዘመን ሊቁ ምላት ሀብቴ የአንኮበር ሚካኤል ሳይሆን ስሙ ያልተጠቀሰ ቤተ ክርስቲያን አለቃ ነበሩ ማለት ነው። በዘመኑ የአንኮበር ሚካኤል አለቃ ያልሆኑበት ምክንያት መምህራቸው አለቃ ወልደ ሐና በሕይወት ስለነበሩ ነው። በዘመኑ አለቅነት ተሾመው እንደነበር አስረጅ የሚሆነውም ክራፐፍ አለቃ እያለ ስለሚጠራቸው ነው። ጣሊያን አገራችንን በወረረች ጊዜ በእንግሊዝ ፓርላማ ብቻ ሳይሆን በመላው አውሮፓ የኢትዮጵያ አፈ ጉባኤ የነበሩት የታዋቂው የታሪክ ምሁር የፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት እናት Sylvia Punkhurst *(1955፣ p.460).* ፤

> *Aleka Wolde Hana, whom the missionaries had found reading st John Chrysostom with Aleka Milat when they paid a visit to his house, now asked them teach him English.The son of Aleka Wolde Serat desired to learn Geography, Like his father. Debtra Habte Selassie applied for teaching in Hebrew, and as he made rapid progress, Aleka Wolde Hana also wanted to learn it. The King's painter came to see the picture books of the missionaries.*

**የአማርኛ ትርጉሙ እንደሚከተለው ነው።**

> *አለቃ ወልደሐና እና አለቃ ምላት ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ሲያነቡ ሚስዮናውያን ያገኟቸው፤ እነርሱም እንግሊዘኛ እንዲያስተምራቸው ጠየቁት (Krapfን)። በወቅቱ የአለቃ ወልደ ሥርዓት (ሥዕርት ይሆን) ልጅ እንደአባቱ ጂኦግራፊ መማር ፈልጎ ነበር። ደብተራ ሀብተ ሥላሴ ዕብራይስጥ ቋንቋ ለማስተማር አመልክተው ነበር፤ፈጣን መሻሻል አሳይተው የነበሩት አለቃ ወልደሐናም ለመማሩ ፈልገው ነበር።የንጉሡ*

*ሠዓሊ የሚሲዮናውያንን በሥዕል ያሸበረቁ መጻሕፍት ለማየት መጥቶ ነበር የሚል ነው።*

Sylvia Punkhurst ለዚህ ኃይለ ቃል ዋቢ ያደረጉት የጀርመናዊውን Krapf ን የጉዞ ማስታወሻ ነው። ጀርመናዊው ወደ አለቃ ወልደ ሐና ጉባኤ ቤት ሲሔድ አለቃ ወልደ ሐና ቁጭ ብለው እየተረጎሙ፣ አለቃ ምላት ደግሞ ቆመው ድርሳን ዘዮሐንስ አፈ ወርቅን ዘሩን እያነበቡ ሲያስተረጉሙ ነው የደረሰው። እንደደረሰም ዕውቀት የማይጠግቡት ሁለቱ ሊቃውንት እንግሊዝኛ እንዲያስተምራቸው ጠይቀውት ነበር። ሊቁ በእምነታቸው ሁለት ልደት በተዋሕዶ ከበረ የሚሉ ስለነበሩ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በተዋሕዶ ከበረ በሚለው እምነታቸው የጸኑትን ሊቃውንት ከአንኮበር ባስወጧቸው ጊዜ እርሳቸውም አንኮበርን ለቀው ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ወደ ሞረት አቡነ ዜና ማርቆስ ሔደው ተቀምጠው እንደ ነበር ገልጫለሁ። ትንሽ ቆይተው ግን ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ተጸጽተው በእንዶዴ ማደሪያ መሬት ሰጥተዋቸው ነበር። ሊቁ በእንዶዴ ማደሪያ የተሰጣቸው በመምህርነት ወይም በሌላ ሙያ መሆኑ ባይገለጥም ሚዛን የሚደፋው የተሰጣቸው ማደሪያ የአለቅነት ይሆናል የሚለው ነው። መተዳደሪያ ተብሎ መገለጡ የደብሩ መዓርግ የአንኮበር ጊዮርጊስን ወይም የአንኮበር ሚካኤልን ያህል ባለመሆኑ መዋረዳቸውን ለመግለጥ ይሆናል። አለቃ ዐምደ ጽዮን ተሰማ (፲፱፻፸፬፣ ገጽ ፲) እንደሚሉት ሊቁ መሬቱን የተቀበሉት ሣህለ ሥላሴ በድርጊታቸው በመጸጸታቸው ካሣ እንዲሆናቸው ነው። አለቃ ምላት ሀብቴ ንጉሥ ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ ከነበሩበት ዘመን የአንኮበር ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን እልቅና ተሾመው እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ ይዘውት ኖረዋል።

## ፰. አለቃ ምላት እንደአስታራቂ ሽማግሌ

አለቃ ለማ ኃይሉ የሊቁን ጥልቅ መንፈሳዊነት የሚተርኩልን በሚከተለው መንገድ ነው። ሚጣቅ አማኑኤል በሚባለው ቦታ የአማኑኤል ጠበል ከሾላ ሥር ይፈልቃል። የተክለ ሃይማኖት ጠበልም ካጠገቡ አለ። ገዳሙን ያቀኑት –ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ“ ብለው ያምኑ የነበሩ ከአማራ ሳይንት የሔዱ መነኰሳት ነበሩ። ሰው እየሔደ ተጠምቆ ከልዩ ልዩ ደዌ ይፈወስ ነበር። ካህናቱ ሦስት ልደት ባይ ስለነበሩ አለቃ ምላት አይወዱቸውም ነበር። መነኰሳቱን ብቻ ሳይሆን ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ተጠምቆ የሚድንበትን የሚጣቅ አማኑኤልን ጠበልም አይወዱትም ነበር። ተጠምቆ ድኖ የተመለሰ ክርስቲያን ወደሳቸው ሔዶ፣

"ጠበል ሔጄ ነበር" ሲላቸው፣

"ወዴት ሔደህ ነበር?" በማለት ይጠይቁታል።

መልሶ፣ "ሚጣቅ አማኑኤል" ሲላቸው፣

–ከእነ እገሌ ውኃ፣ ከሳይንቶቹ ከነአባ ወልደ ሃይማኖት ውኃ ሔደህ ነበር?" እያሉ ይቀልዱ ነበር። ወገኖቻቸውን አትሒዱ በማለት ይከለክሉም ነበር። አለቃ ምላት ጸሎተኛ መሆናቸው በአገር የታወቀ ስለነበር ከዕለታት አንድ ቀን ሌሊት ቀደም ብለው ተነሥተው ዳዊቱን እና መልክአ መልክኡን ደግመው ጨርሰው እንደ ተቀመጡ እንቅልፍ እንደ አሸለባቸው የተፈጸመውን አለቃ ለማ ኃይሉ (በመንግሥቱ፣ ፲፱፻፺፱፣ ገጽ ፻፳፪- ፻፳፬) የገለጡት፡-

> ዙፋን ተዘርግቶ፣ ንጉሡ ተቀምጦ እነሚካኤል እና እነ ገብርኤል ያስጠምቃሉ። ብቅ ስል ጊዜ ይህን ትዕቢተኛ አባረህ መልሰው በማለት ንጉሡ ሲናገር ይዘው ሲያንገላቱኝ ብንን አልኩ። አንተ በምሕረትህ ለፍጥረትህ ያደረግኸውን ቸርነት እነዚያን ነቀፍን ብለን በማለት ሔጄ ከጠበሉ ተጠምቄ መጣሁ።እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ራርቶ ውኃውን መድኃኒት አድርጎ ሲሰጥ እኔ ለዚህ በተአምራት ተጠምቆ ለሚድነው ሁሉ ምቀኛ ሆኜ ኖሯል ብለው ተናገሩ። ከዚያ በኋላ ሚጣቅ ሔዶ አንድ ቀን ያልተጠመቀ እንዳይኖር ብለው በመናገራቸው ሁሉም ሔዶ ተጠመቀ። ሰው ሔዶ ራሴን ያመኛል፣ ሚስቴ እንዲህ ሆና ሲላቸው ሔደህ ሚጣቅ አማኑኤል ተጠመቅ፣ የታመመች ሚስትህን ሚጣቅ ውሰዳት ይሉ ጀመር።

በማለት ነው። የተጠቀሰው ነገር በተፈጸመበት ዘመን አለቃ ወልደ ያሬድ ከአለቃ ምላት ፍትሐ ነገሥት ይማሩ ስለነበር፣ ተማሪዎች ሊማሩ ሲሔዱ ጌቶች የሉም ይሏቸዋል። ተማሪዎቹም መልሰው የት ሔዱ? ሲሏቸው የአለቃ ምላት ቤት ሰዎችም ሚጣቅ በማለት ይመልሳሉ። ተማሪዎች ደግመው፣ –አለቃ ምላት ሚጣቅ ይሔዳሉን? ወደ ንጉሥ ምኒልክ ተጠርተው ሔደው ይሆናል" ብለው ወደ የቤታቸው ተመልሰዋል። አለቃ ምላት ስለሚፈሩ እንኳን ሴት ወንድ ዓይኑን ሞልቶ ስለማያያቸው አለቃ ምላት መጡ ሲባል ይጠመቅ የነበረው ሁሉ ልብሱን እየጣለ ርቃኑን ይሸሻል። እርሳቸው ወደ ጠበሉ ቀረብ ብለው በእጃቸው ፊታቸውን ርጨት ርጨት ካደረጉ በኋላ ይጠመቅ የነበረውን ሰው ሁሉ እግዚአብሔር ምሕረቱን ያምጣላችሁ ብለው እልፍ ብለው አሽከሮቻቸውን ተጠመቁ ይላሉ። አለቃ ምላት መጡ መባልን የሰሙት የገዳሙ መነኰሳት እንጀራውን፣ ጠላውን፣

ጠጁን፣ ዳቦውን፣ ቆሎውን ይዘው ቀርበው እህል ይብሉልን ብለው ይለመኗቸዋል። ሊቁም እግዚአብሔር ይስጣችሁ ብለው መርቀው ተመልሰው አንኮበር ገብተው አድረዋል። በበነጋው ማለዳ ጌቶች መጥተዋል በማለት የአለቃ ምላት አሽከር ወደ አለቃ ወልደ ያሬድ ሔዶ መልእክት ይናገራል። መልእክተኛውም አለቃ መጥው አድረዋል ብሎ ሲነግራቸው አለቃ ወልደ ያሬድ ተነሥተው ወደ አለቃ ምላት ይሔዳሉ። ትናንት ወዴት ሔደው ነበር? ሲሏቸው እግዚአብሔር በመሐሪነቱ ለፍጥረቱ አዝኖ እና ራርቶ የሠራውን ሥራ እነአባ ወልደ ሃይማኖትን ነቀፍን ብለን የሚጣቅን ጠበል እየነቀፍን ይኸውልህ እንዲህ ያለ ሕልም አየሁ።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ አለቃ ምላት[1] በ፲፰፻፸ ዓ.ም. ንጉሥ ምኒልክ እና ነገሥቱ ለዐፄ ዮሐንስ ለጦርነት ሲዘጋጁ የክርስቲያን ደም በከንቱ አይፍሰስ ብለው ያስታረቋቸው ፈሊጠኛ መሆናቸው የተመሰከረላቸው ሊቅ በመሆናቸው ነው። ዐፄ ዮሐንስ የካቲት አምስት ቀን ፲፰፻፸ ዓ.ም. በመንዝ በኩል አልፈው በይጣ ቅዱስ ሚካኤል ከተባለው ቤተ ክርስቲያን አጠገብ መስፈራቸው ይሰማል። በዚህ ጊዜ አለቃ ምላት የአንኮበር ሚካኤልን፣ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ የአንኮበር መድኃኔዓለምን፣ አለቃ እሸቱ የአንኮበር ማርያምን፣ አለቃ ኪዳነ ማርያም የአንኮበር ጊዮርጊስን ታቦቶች አስይዘው ሥዕል እና መስቀል አስቀድመው ወደ ዐፄ ዮሐንስ ሔደው ወደራ ከሚባል ቦታ ላይ አገኟቸው። ዐፄ ዮሐንስ አለቃ ምላትን በሩቁ ሲያዩዋቸው ከበቅሏቸው ወረዱ። ንጉሡ እስከ ነበሩበት ቦታ እንዲሔዱም አጋፋሪያቸውን ወደ አለቃ ምላት ላኩባቸው። በእንደዚህ ዓይነት ሥርዓት አለቃ ምላት ወደ ዐፄ ዮሐንስ ገብተው ተገናኙ። ሊቁ አለቃ ምላት ፈሊጥ ዐዋቂ ስለነበሩ "ጌታዬ ከሁሉ አስቀድሞ አንድ ነገር አስቸግሮኛል፤ አንተ እንዳልል እግዚአብሔር ቀብቶ ያነገሠህ ነህ፤ እርስዎ እንዳልል ገና ልጅ ነህ" አሉ። በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ "አባቴ ፈቅጀልዎታለሁ አንተ ይበሉኝ" በማለት ተናገሩ። አለቃ ምላትም ለእኔም ይስማማኛል ብለው በመቀጠል "ጌታዬ ምኒልክን ታረቀው አንተ የታዘዝከው ሃይማኖት እንድታጸና፣ ቤተ ክርስቲያንን እንድታቀና ነው" ብለው የብቃት አነጋገር ጨምረው ነገሯቸው። አለቃ ምላት ማንንም ቢሆን እርስዎ ብለው አይጠሩም ነበር ይባላል (አድማሱ፣ ፲፱፻፷፫ ዓ.ም፣ ፪፻፲፫) ። አለቃ ምላት ዐፄ ዮሐንስን "አንተ የታዘዝከው (የነገሥከው) ሃይማኖት እንድታጠና፣ ቤተ ክርስቲያን እንድታቀና ነው" በማለት የተናገሯቸው በዘመኑ በሸዋ ሦስት ልደት የጸጋ ልጅ ብለው ያምኑ የነበሩት ጊዜ ሰጥቷቸው፣ በተዋሕዶ ከበረ ብለው ያምኑ የነበሩት ከሸዋ ተሰድደው የነበረ በመሆኑ ሊሆን ይችላል።

አለቃ ምላት ዐፄ ዮሐንስን ጌታዬ ምኒልክን ታረቀው ሲሏቸው ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ

[1] ዋናውን ለመናገር እንጂ እነ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ፣ በወቅቱ መምህር አካለ ወልድ መኖራቸው አልተገለጠም፣ እነ አለቃ እሸቱ በዕርቁ ላይ መሳተፋቸው የማይዘነጋ ነው።

ዮሐንስ "እኔ ተበድዬ መጣሁ እንጂ ምን አጠፋሁ? በጌምድር ድረስ እየመጡ እኔ የምገዛውን አገር አዘረፉብኝ። እንታረቅም ብዬ ብልክባቸው አሻፈረኝ አሉ" በማለት ንጉሠ ነገሥቱ ላቀረቡላቸው ስሞታ የአለቃ ምላት መልስ "እንደ አንተ ያለ ሰው ሳይበደል ይነሣል! ተብሎ ነው እንዴ" የሚል ነበር።ይህ የዐፄውን ጽኑ ሃይማኖተኛነት የሚያረጋግጥ ንግግር ነው። ንጉሡም በአለቃ ምላት ዐሳብ የተስማሙት ብዙ ሳያስቸግሩ ነበር። "ወዲያውም በደብረ ብርሃን የዕርቅ ድርድር ተጀምሮ ንጉሠ ነገሥቱን እና ንጉሡን መጋቢት ፲፰ ቀን ፲፰፻፸ ዓ.ም. በመሐላ አስታረቋቸው" (አድማሱ፣፲፱፻፰፫፣ ፪፻፲፫) የሚለው የአድማሱ ጀምበሬ ጽሑፍ መጠነኛ እርማት ያስፈልገዋል። የሁለቱ አካላት ዕርቅ የተፈጸመው ከየካቲት ፲፰ ቀን ፲፰፻፸ ዓ.ም. በፊት ሲሆን መጋቢት ፲፰ ቀን ፲፰፻፸ ዓ.ም ዐፄ ዮሐንስ ለንጉሥ ምኒልክ ዘውድ የደፉበት ዕለት ነው (ገብረ ሥላሴ፣ ፲፱፻፶፱፣ ገጽ ፹፮)።

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ (፲፱፻፶፱፣ ገጽ ፹፪) ታሪኩን የጻፉት፤

> *ከአንኮበር ቅዱስ ሚካኤል አለቃ ምላት፣ ከመድኃኔ ዓለም አለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ካህናቱን፣ ሥዕሉን፣ መስቀሉን ይዘው ወደ ንጉሥ ምኒልክ ሔደው በክርስቲያን ንጉሥ ጊዜ የክርስቲያን ደም አይፍሰስ። የፍቅር አምላክ የሆነው እግዚአብሔር በቸርነቱ ለዕርቅ ቢረዳ ወደ ዐፄ ዮሐንስ መሔዳችን ነውና ይፍቀዱልን አሏቸው። ንጉሥ ምኒልክም እኔስ የክርስቲያን ደም ቢፈስ መች እወዳለሁ። ዕርቅንስ ለምን እጠላለሁ። ከሆነላችሁ ሒዱ ብለው አሰናበቷቸው። ወደ ዐፄ ዮሐንስ የሔዱት ሊቃውንት ወደራ ከተባለ ቦታ ላይ ሰፍረው አገኟቸው። ዐፄ ዮሐንስም ካህናቱን ተናግረው ቃሉን ነግረው (የሚታረቁ መሆናቸውን በቃል ጭምር ተናግረው) ሰደዷቸው። በዚህ ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ ታቦተ ጽዮን ለእስራኤል መመኪያ እንደሆነቻቸው ለእኔም ትሁነኝ ብለው ከድንባሮ ታቦተ እግዝእትነ ማርያምን አስመጥተው ለጦርነት ተዘጋጅተው ስራቲ ላይ ሰፈሩ። ነገሩንም በእግዚአብሔር ላይ ጥለውት ለዕርቅ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ሔደው የነበሩት ሰዎች እስከሚመለሱ ድረስ ሠራዊታቸው ከቍጥጥር ውጭ ሆኖ ጦርነት እንዳይገጥም እየከለከሉ ቆዩ::*

በማለት ነው። *በወቅቱ ንጉሠ ነገሥቱ መጀመሪያ ላለመታረቅ ፈልገው እንደ ነበር* አመላካች ነው። ለመታረቅ ፈቃደኛ የሆኑበትን ምክንያት የገለጡትም በሚከተለው መንገድ ነው።ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ (፲፱፻፶፱፣ ገጽ ፹፫) ፤

> *ዐፄ ዮሐንስ ግንባሮ ሜዳ ላይ ሔደው ሲሰፍሩ ወራሪያቸው በሬሳን ተሻግሮ ዘለቀ። በዚህ ጊዜ የሸዋ ፈረስ ዓይን ለዓይን ሲተያይ መታገኛ ጠፋበት። ጥቂት ፈረስ ዘልቆ ገጠመው፤ አስመልሶ ድንባሮ አስገብቶት ተመለሰ። በዚያን ጊዜ ከትግሬ ብዙ ሰው አለቀ። ከዐፄ ዮሐንስ ሰዎች ብዙዎቹ በመሞታቸው እና በመቁሰላቸው የዐፄው ጦር ደነገጠ። ድንጋጤውን የጨመረው ለሸዋ ጦር ግዳይ መጣል እንጂ መማረክ አያውቅም ተብሎ መወራቱ ነበር። ይህም እንደገና ዕርቅ እንዲጀመር ምክንያት ሆነ። ንጉሥ ምኒልክ ከዐፄ ዮሐንስ ላይገቡ፣ ጠላት በተነሣባቸው ጊዜ ጦር ሰደው ሊረዱ ስምምነት ተደረገ። በአቡነ ተክለ ሃይማኖት መስቀል፣ በጽላተ ሙሴ ጻሕል እና ጽዋዕ ዐፄ ዮሐንስን ከነመኳንንቶቻቸው አስምለው አስገዙቱ ብለዋል።*

አድማሱ ጀምበሬ በንጉሠ ነገሥቱ እና በንጉሡ መካከል በተፈጸመው ዕርቅ የደብረ ብርሃን ካህናት መሳተፋቸውን ሲነግሩን ሥርግው ግን በአንኮበር የሚገኙት የአራት አድባራት ሊቃውንት መሆናቸውን በስም ዘርዝረው ጽፈዋል። ጉባኤው ደብረ ብርሃን ላይ ተካሔዶ የደብረ ብርሃን ሊቃውንት አይኖሩበትም ማለት ስለማይቻል የአድማሱ ጀምበሬ አሳብ ወደ እውነቱ ይጠጋል።አለቃ ምላት ያረፉት አለቃ ለማ ኃይሉ መምህራቸውን አለቃ "ተጠምቆ" ን ይዘው ከጎጃም ደብረ ሊባኖስ ገብተው ትንሽ ቀን ካረፉ በኋላ የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን አለቃ የነበሩት ማን መልሶህ ወልደ ሥላሴ ክፉውን ቀን ከእኔ ዘንድ አሳልፉት ብለው ይዘዋቸው በሔዱበት ዘመን አካባቢ ነው። ይህም በ፲፰፻፹፭ ዓ.ም. መጨረሻ ወይም ፲፰፻፹፮ ዓ.ም መጀመሪያ አካባቢ ሊሆን ይችላል። አለቃ ለማ ከደብረ ብርሃን አንኮበር በወረዱ ጊዜ አለቃ ምላት በሕይወት እንዳልነበሩ ነግረውናል። አለቃ ለማ አንኮበር የሔዱት የካቲት ፲፰፻፹፫ ዓ.ም. ነው። አለቃ ገብረ መድኅን አንኮበር ሔደው በ፲፰፻፹፭ ዓ.ም. አካባቢ ትምህርት እንደ ጀመሩ አለቃ ምላትን አግኝተዋቸው ከቤታቸው ኃብዘዋቸዋል።

በሌላ በኩል በ፲፰፻፹፭ ዓ.ም. መጨረሻ ወይም በ፲፰፻፹፮ ዓ.ም. መጀመሪያ ከደብረ ሊባኖስ ለትምህርት አንኮበር የሔዱት አለቃ ገብረ መድኅን በአንድ የሰንበት ዕለት አንኮበር ሚካኤል ዕጣነ ሞገሩን ሲመሩ የሰሙት አለቃ ምላት በጣም ተደስተው ከቤታቸው ወስደው ኃብዘዋቸው እንደነበር አለቃ ለማ (መንግሥቱ ፣፲፱፻፶፱፣ ገጽ ፻፬-፻፮) የገለጡት እንዲህ በማለት ነበር፤

*እግዚአብሔር ገብረ መድኅንን የመሰለ ድምፃዊ አልፈጠረም። ይኖሩ የነበረው አንኮበር ሚካኤል ከመቃብር ቤት ነበር። ዜማ ነጋሪው አባትሁን ይባል ነበር። ቀስ በቀስ ከአለቃ ገብረ መድኅን ጋር ተለማመዱ። የአንኮበር ሚካኤል አለቃ ቅኔ ዐዋቂ የነበሩት ታላቁ አለቃ ምላት ነበሩ። በአዘቦት ቀን ይቅርና በዕለተ ሰንበት እንኳ ቢሆን ቅኔ መቀኘት2 ያሰኛቸው ነበር። ከቅዳሴ በኋላ መወድስ ሲባል አባትሁን ኢያ ገብረ መድኅን ተመራ ሲላቸው አለቃ ምላት የሚቀኙት ቅኔ የሚበላሽባቸው ስለመሰላቸው ቅር ተሰኝተው ነበር። ገብረ መድኅን ቅድስት ስለነበሩ ዜማውን ቀስ ብለው ጀምረው ሲለቁት ጊዜ አለቃ ምላት በደስታ ሊሞቱ። ገብረ መድኅንም ተመልሰው ቅድስት ገብተው ተቀመጡ። አለቃ ምላት ከደስታቸው ብዛት የተነሣ እየደጋገሙ እንዴት አሳመረው እያሉ ቆዩ። ዕጣን ሞገር ተቆሞ ሲያበቃ አለቃ ምላት ቅኔ የተቀኘውን ሰው ጥሩት ብለው አስጠርተው ከቤታቸው ይዘዋቸው ሔዱ። ምሳቸውን እያበሉ አገርህ የት ነው ብለው ሲጠይቋቸው ትግሬ ብለው መለሱ። አሁን ያለኸው የት ነው? ብለው ሲጠይቋቸው መድኃኔ ዓለም ከነአለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ዘንድ ብለው መለሱላቸው። ትግሬ ሆነህ ከሦስት ልደቶች ከመድኃኔ ዓለም ምን ወሰደህ? ሲሏቸው ሐዲሳት የሚያስተምረኝ በተዋሕዶ የሚያምን መምህር ባጣ ብለው መለሱላቸው። አለቃ ምላትም ሐዲሳት የሚያስተምር ወልደ አማኑኤል የሚባል ወንድምህ ከጎንደር ተምሮ መጥቷል። ከእርሱ ዘንድ ተማር ብለዋቸው ገብረ መድኅንም ጎንደር ከተማ በምትገኘው ግምጃ ቤት ማርያም ወንበር ዘርግተው ያስተምሩ ከነበሩት ከመምህር ወልደ ሚካኤል ተምረው ተመልሰዋል" ስለአሏቸው አፈር ባይኔ ተክለ ሃይማኖት ገብተው ያስተምሩ ከነበሩት ከቡልጋው ተወላጅ ከወልደ አማኑኤል ዘንድ መማር ጀመረዋል።*

የአለቃ ለማ ንግግር የአንኮበር ሚካኤሉን አለቃ ምላትን በአካል ባያገኟቸውም እስከ ፲፰፻፹፩ ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በሕይወት ለመኖራቸው አስረጅ ሆኖ የሚጠቀስ ነው። በ፲፰፻፹፩ ዓ.ም. መጀመሪያ አካባቢ አለቃ ወልደ አማኑኤል ከጎንደር በመጻሕፍተ ሐዲሳት ተመርቀው አንኮበር ገብተው ወንበር ዘርግተው ማስተማር የጀመሩበት ዘመን መሆኑን አለቃ ምላት መናገራቸውን አለቃ ለማ ገልጠዋል። አለቃ ለማ በአለቃ ምላት አልደረስኩባቸውም በማለት መናገራቸው አለቃ ለማ ደብረ ብርሃን ቢገቡም አንኮበር ሳይሔዱ በመቅረታቸው ሊሆን ይችላል። በዘመኑ ለትምህርት አንኮበር

[2] ሊቁ ለማ ኃይሉ እንዲህ ያሉት ወንበር ዘርግተው፣ ቅኔ ለማስተማር ይፈልጉ ነበር ለማለት ነው። መቀኘትማ በየሰንበቱ ዕለት ከቅዳሴ በኋላ የሚቀርበውን ቅኔ ለሌላ ሊቅ አይሰጡም ነበር ብለዋል።

ሔደው የነበሩት አለቃ ገብረ መድኅን አለቃ ምላትን መተዋወቃቸውን አለቃ ለማ ነግረውናል። አለቃ ገብረ መድኅን መጻሕፍት ሐዲሳትን ለመማር የሔዱት ከነአለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ቢሆንም የተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑት ወልደ አማኑኤል ከጎንደር መምጣታቸውን ነግረው ከእርሳቸው እንዲማሩ ያደረጉት አለቃ ምላት ናቸው። አለቃ ወልደ አማኑኤል ከጎንደር ተምረው አንኮበር የገቡት ጎንደር በ፲፰፻፹፩ ዓ.ም. በደርቡሽ ከመቃጠሏ ቀደም ብሎ ነው። ከዚህም በዚህ ዘመን አለቃ ምላት በሕይወት እንደ ነበሩ ማሳያ ነው።

በዚህ ዘመን አለቃ ገብረ መድኅን አንኮበር መጻሕፍት መማር ከጀመሩ ከአለቃ ምላት የተዋወቁትም፣ ትምህርት የጀመሩትም በዚያው ዓመተ ምሕረት መጀመሪያ ወይም አጋማሽ አካባቢ ትምህርት ጀምረዋል ማለት ነው። አለቃ ለማ የሐዲሳት እና የሃይማኖተ አበው መምህራቸውን አለቃ ገብረ መድኅንን ደብረ ሊባኖስ ያገኟቸው በትምህርት ላይ ቢሆኑም ግንቦት ፲፪ የሚከበረውን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት አጽም የፈለሰበትን ዕለት ለማክበር ሄደው ሊሆን ይችላል።  አለቃ ገብረ መድኃን በወርኃ ግንቦት ፲፰፻፹፩ ዓ.ም. ትምህርት ካልጀመሩ ትምህርት ጀምረው አለቃ ምላትን ሊተዋወቋቸው የሚችለው በ፲፰፻፹፩ዓ.ም. ክረምት ወይም በ፲፰፻፹፪ ዓ.ም መጀመሪያ ነው። ከዚህ ተነሥተን አለቃ ምላት እስከ ፲፰፻፹፩ ዓ.ም. መጨረሻ ወይም ፲፰፻፹፪ ዓ.ም. በሕይወት ነበሩ ማለት እንችላለን። አለቃ ለማ በ፲፰፻፹፩ዓ.ም. ክረምት ደብረ ብርሃን ቢሔዱም ከአለቃ ምላት ጋር ሳይተዋወቁ የቀሩት እርሳቸው መስከረም ወር ፲፰፻፹፪ ዓ.ም. ታመው ስለነበር ወደ አንኮበር ባለመሔዳቸው እንጂ አለቃ ምላት ከዚያ በፊት በማረፋቸው አይመስልም። አለቃ ምላት ቅኔ ዐዋቂ በመሆናቸው ከቅዳሴ በኋላ ከእርሳቸው ውጭ ሌላ ሊቅ እንዲቀኝ የማይፈቅዱ፣ እንኳን በአዘቦት በዕለተ ሰንበትም መቀኘት ያሰኛቸው እንደ ነበር ይነገርላቸዋል። ሊቃውንት በሰንበት ጉባኤ ባይዘረጉም ለቅኔ የነበራቸው ፍቅር በሰንበት ለማስተማር ይገፋፋቸው ነበር ለማለት ነው። የአለቃ ምላት ሀብቴን የሕይወት ታሪክ በተመለከተ ጥናት ያደረኩት አበርክቷቸው ከፍተኛ በመሆኑ ነው። አበርክቷቸው ሲገለጥ የኖረውም በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በቤተ መንግሥት ጭምር ነው።  ዕድሜ ልካቸውን ወንበር ዘርግተው በአንድ በኩል በቃላቸው ቅኔ፣ መጻሕፍተ ብሉያት፣ መጻሕፍተ ሐዲሳት እና ፍትሐ ነገሥት ሲያስተምሩ በሌላ በኩል ደግሞ የመጻሕፍት ተማሪ ዞሮ እየለመነ መማሩ የትምህርት ጊዜውን ስለሚሻማበት ካላቸው እየከፈሉ የዕለት ምግባቸውን ይመግቧቸው ነበር።  እንዲህ ያለው ተግባር የተማሪንና የመምህርን ሕይወት በእጅጉ የተቆራኘ እንደሚያደርገው መታወቅ አለበት።

አለቃ ምላት ወንበር ዘርግተው፣ ጉባኤ አስፍተው ሲያስተምሩ የኖሩ ሊቅ በመሆናቸው ለቤተ ክርስቲያን ተተኪ ሲያፈሩ ኖረዋል። በነገሥታት ፊት ርትዕ የሆነ ፍርድ የሚሰጡ መምህራንን ሲተኩ መኖራቸውምአበርክቷቸው በቤተ ክርስቲያን የተወሰነ ሳይሆን ለአገርም የተረፈ ነበር። በቦሩ ሜዳ በተካሄደው የሦስት ልደት እና የሁለት ልደት ክርክር ጊዜ ዋና አስተናባሪ እና ሊቃውንቱን በተገቢ መዓርግ ያስቀምጡ የነበሩት አለቃ ወልደ ያሬድ ከእርሳቸው እስከ ፍትሐ ነገሥት ያለውን የትርጓሜ ትምህርት የተማሩ ሊቅ መሆናቸውን አለቃ ለማ ኃይሉ በመጽሐፈ ትዝታቸው ተናግረዋል። ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከእልቅና ባነሷቸው ዘመን የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ የነበረው ክራፕፍ አንኮበር የነበረ ቢሆንም ቸገረኝ ብለው ወደ እርሱ ሃይማኖት ከመሳብ ይልቅ እርሱን አስተምረው ወደ ትክክለኛው ሃይማኖት ለማስገባት ያደርጉት የነበረው ሙከራ የሚያስደንቅ ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ ከግብፅ ካስመጧቸው ጳጳሳት አንዱ የነበሩትን አቡነ ማቴዎስን ለንጉሥ ምኒልክ በሰጧቸው ጊዜ ለጳጳስ የሚመጥን ቤት ያልነበራቸው ንጉሥ እንዳይነወሩ የሞላ ቤታቸውን የለቀቁላቸው ፍቅረ ንዋይ የራቀላቸው በመሆናቸው ጭምር ነው። ከዚህ በተጨማሪም ዋናውና በዘመናችን በአገልግሎት ላይ የሚገኙ አባቶች አብነት ሊያደርጉት የሚገባው ተግባራቸው ንጉሠ ነገሥቱ ዐፄ ዮሐንስ እና የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ለጦርነት በተሰላለፉ ጊዜ የክርስቲያን ደም በከንቱ አይፍሰስ ብለው፣ በፈሊጥ ዐዋቂነታቸው አስማምተው ዕርቅ ያወረዱ ሊቅ መሆናቸውን አብነት ማድረግ ነው።

# መደምደሚያ

አለቃ ምላት ሀብቴ በ፲፰ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ በቀድሞው ሸዋ ጠቅላይ ግዛት በሞረት ዜና ማርቆስ አካባቢ ተወልደው፣ በትውልድ አካባቢያቸው የመጀመሪያ ደረጃ የሆነውን የቃል ትምህርት ተምረዋል። በመቀጠልም በዘመኑ የሸዋ ነገሥታት መቀመጫ ወደ ነበረችው አንኮበር በመሄድ ቅኔና አራት ዓይና ከነበሩት ሊቅ ከአለቃ ወልደ ሐና ትርጓሜ መጻሕፍትን ተምረዋል። ቅኔና ትርጓሜ መጻሕፍት ተምረው በመምህርነት ከተመረቁ በኋላ ስሙ ባልተገለጠ አንድ ደብር እልቅና ተሾመው፣ ወንበር ዘርግተው ሲያስተምሩ ቆይተው፣ ፲፰፻፴፩ ዓ.ም. ጥር ወር አካባቢ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከእልቅና ሽረዋቸው፣ ወንበራቸውን አጥፈው ለጥቂት ጊዜ ለብቻቸው ቆይተዋል።

ከሦስት ዓመት በኋላ ደግሞ ጥቅምት ወር ፲፰፻፴፬ ዓ.ም. የተዋሕዶ ሊቃውንት ከአንኮበር በተሰደዱ ጊዜ እርሳቸውም ተሰደው ወደ ትውልድ ቦታቸው ሞረት አቡነ ዜና ማርቆስ ሔደው ነበር። አለቃ ምላት ሀብቴ ለዳግማዊ ምኒልክ መወለድ ምክንያት መሆናቸውን አለቃ ለማ ኃይሉ ገልጠዋል። ከአንኮበር ተሰደው በሞረት ዜና ማርቆስ ጥቂት እንደቆዩ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ በድርጊታቸው በመጸጸት እንዶዴ ተክለ ሃይማኖት ላይ ሾመዋቸዋል[3]። ዐፄ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ በኋላ አቡነ ሰላማ ሊቁን የሸዋ ጠቅላይ ግዛት ሊቀ ካህናት አድርገው ሾመዋቸው የነበረ ቢሆንም በጸጎች ተጽዕኖ ሹመቱን ሳያገኙ ቀርተዋል።

ከእልቅናቸው ቢሻሩም ችግር አገኘኝ ብለው ሃይማኖታቸውን ሳይቀይሩ ጸንተው የኖሩ ሊቅ ናቸው። ዳግማዊ ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ ከሆኑ በኋላ ግን እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ በአገለገሉበት አንኮበር ሚካኤል እልቅና ተሾመው በአንድ በኩል ወንበር ዘርግተው እያስተማሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ንጉሥ ምኒልክን እያማከሩ ኖረዋል። ሊቁ ብዙ መልካም ነገሮችን ያከናወኑ ቢሆንም በ፲፰፻፸ ዓ.ም. ለጦርነት ተሰላልፈው የነበሩትን ንጉሥ ምኒልክንና ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዮሐንስን አስታርቀው የክርስቲያን ደም እንዳይፈስ ማድረጋቸው ግን ጎልቶ የሚነሳ ተግባራቸው ነው። የንግግር ፈሊጥ እንደሚያውቁ የሚነገርላቸው አለቃ ምላት ሀብቴ አገራቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን ሲያገለግሉ ኖረው ዳግማዊ ምኒልክ ዘውድ ደፍተው ከመንገሣቸው ከጥቂት ወራት በፊት ከዚህ ዓለም ተለይተዋል።

[3] እንዶዴ ተክለ ሃይማኖት ከአንኮበር ከተማ በግምት እስከ ዐሥር ኪሎ ሜትር የሚርቅ፣ ከሎዛ ሚካኤል ወረድ ብሎ ወደ በረሃው የሚገኝ፣ በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የተተከለ ደብር ነው።

## ማጣቀሻ ጽሑፎች


መንግሥቱ ለማ። (፲፱፻፶፱)። *መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ።* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላማ ማተሚያ ድርጅት።

ማኅበረ ቅዱሳን። (፳፻፲፩)። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥናት መጽሔት ቁትር ፯።

ሣህለ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም። (ግንቦት ፲፱፻፺፱)። "ባዮግራፊና ኦቶባዮግራፊ"፣ *ብሌን መጽሔት*፣ ቁ.፬።

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ። (፲፱፻፸፱)። *አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት* (ያልታታመ)። ቅጽ 2።

________________። (፲፱፻፹፩)። *አማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ፩።* በምዕራብ ጀርመን በከፍተኛ መንፈሳዊ ት/ቤት ከሚማሩ ኢትዮጵያውያን የተዘጋጀ፣ ሃይድል በርግ።

______________። *ዳግማዊ ምኒልክ የዘመናዊነትፈር ቀዳጅ።* (የታተመበት ቦታና ዘመን ያልተገለጠ)።

በአማን ነጸረ። (፳፻፲፮)። *መዋዕያን ተኀሥሦ* ቅጽ ፪። አዲስ አበባ፣ ጃጃው አታሚዎች።

ኅሩይ ወልደ ሥላሴ። (፲፱፻፲፭)። *የሕይወት ታሪክ።* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላማ ማተሚያ ቤት።

አድማሱ ጀምበሬ። (፲፱፻፸፫)። *መጽሐፈ ቅኔ ዝክረ ሊቃውንት።* ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

የኢ/ኦ/ተ/ ቤ/ክ/። (፲፱፻፹፩)። *ትንሣኤ መጽሔት።* ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ደርጅት፣ቊጥር፶።

ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ። (፲፱፻፶፱)። *ታሪከ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት_ዘኢትዮጵያ።* ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

Abrams, M.H. (1999). *A Glossary of Literary Terms* .7th Ed. USA: Helnle & Heinle.

Cuddon, J.A. (1977). *A Dictionary of Literary Terms*. London: Andre Deutsch.

Krapf, Johann Ludwig. (1860). *Travels, Researches and Missionry Labours durying an eighteen years Residence in East Africa*. London.

Pankhurst, Sylvia. (1955). *Ethiopia: A Cultural History.*London, Leightonstraker book-binding co. Ltd.

TadrosY.Malaty. (1993). Lectures in Patroalogy the Apostolic Fathers.St. George's Coptic Orthodox Church Sporting- Alexandria Egypt.